የከ/መ/ቁ 282979
ጥቅምት 12 ቀን 2013 ዓ/ም

ልደታ ምድብ 4ኛ ንግድ ችሎት

ዳኛ፡- መካ ነስሩ

ከሳሾች፡- 1/ አቶ ሰለሞን ገ/ኪዳን ገ/ጻዲቅ

2/ አቶ አድነው በቀለ ንጋቱ ጠበቃ ገ/ሚካኤል ወልዱ ቀረቡ

ተከሳሾች፡- 1- አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- ጠበቃ አብይ መኮንን ቀረቡ

2 - አቶ ንጋቱ አበበ አሰን

3 - አቶ ናርዶስ ወርቁ በየነ ጠበቃ አብይ መኮንን ቀረቡ

4 - አቶ ብርሃኑ ዘኑ ቱፋ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በማህበር ላይ የመፍረስ ውሳኔ መስጠትን የተመለከተ ሲሆን የከሳሾች ጠበቃ በጥር 29 ቀን 2012 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከሳሾች ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን በህዳር ወር 2010 ዓ/ም 1ኛ ተከሳሽ ድርጅት መስርተን ስራ እየሰራን እንገኛለን፡፡አምስታችንም የድርጅቱ መስራችና አባላት በስራው እኩል ሙያዊ አስተዋፅኦ ስለምናደርግ የምናገኘው ጥቅም በቦነስ በወርሐዊ ደመወዝ እና በመጨረሻ ከሚገኘው የትርፍ ክፍፍል/ዲቪደንድ/ የሚካካስ የቅድመ-ክፍያ/አድቫንስ/ እንዲሆን ተስማምተናል፡፡በሂደት ግን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ከስምምነታችን ውጪ እና ከሳሾችን በሚጎዳ መንገድ ድርጅቱ ከሚያገኘው ገንዘብ የበለጠ/እጥፍ/ ቅድመ--ክፍያ/ጥቅማጥቅም ለግላቸው እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡

ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ከ1ኛ ተከሳሽ ድርጅት ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰራ ሌላ አዲስ ድርጅት በመክፈት የ1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱ ደንበኞች የአዲሱ ድርጅት ደንበኞች እንዲሆኑ አድርጓል፣የ1ኛ ተከሳሽ ድርጅት ንብረትና ሀብት ብሎም ሰራተኞች በአዲሱ ድርጅት አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ግልፅ የሆነ የጥቅም-ግጭት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ፣ድርጅቱ ከተመሰረተ ጀምሮ እስከ አሁን የአባላት ስብሰባ ጠርተው አያውቁም፣ስብሰባ ተድርጎ አያውቅም፣የስራ ሪፖርት ቀርቦ አያውቅም፤አጠቃላይ በአሰራር ስርዓት ዙሪያ መመካከር፣አቅጠጫ ማስቀመጥ አልተደረገም፣ብቁ አመራር አልተሰጠም፣ሰራተኞች በአግባቡ የማሰማራት ስራ አይሰራም፣የገንዘብ አጠቃቀም እና ፍሰቱ የሚመለከት ግልፅ የአሰራር ሥርዓት የለም፣ኦዲት ስለማይሰራ የትርፍ ክፍፍል መረጃ የለም፣የትርፍ ክፍፍልም ተደርጎ አያውቅም፡፡

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አልተሰራለትም፣2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች የድርጅቱ ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው እያዋሉ ባለበት ሁኔታ የታህሳስ ወር 2012 ዓ.ም. ወርሓዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ለመንግስት አልተከፈለም፡፡

7.የድርጅቱ የባንክ ሂሳብ መግለጫ/ባንክ እስቴትመንት/ ለአባላት አይገለፅም፣ለውስጥ ኦዲተርም መረጃው በአግባቡ አይደርስም፡፡

8.ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች በመመሳጠር እና ለአባላት ሳያሳውቁ እስከ ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር ከድርጅቱ ወስደው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል፡፡ከዚህም በላይ በየጊዜው ቁጥሩ በትክክል የማይታወቅ ገንዘብ ከድርጅቱ ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ያውላሉ፡፡

9.ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ከቅን-ልቦና ውጪ፣ለአባላት አስቀድሞ ስብሰባ እንደሚደረግ ሳያሳውቁ፣በድንገትና ተመሳጥረው፣በድርጅቱ የሚያደርጉት ያለው ጥፋት ወይም የገንዘብ ብክነት ለመሸፈን እንዲረዳቸው በማሰብ በታህሳስ 07 ቀን 2012 ዓ.ም. ስብሰባ በመጥራት ድርጅቱ ይፍረስ የሚል ቃለ-ጉባኤ በመያዝ በአብላጫ ድምፅ (የከሳሾች አነስተኛ ድምፅ ነው)

ወስኗል፡፡ነገር ግን የድርጅቱ ስራ፣ሕልውና፣የአባላት ጥቅም በሚፃፀረር መልኩ የተያዘው ቃለ-ጉባኤ በሚመለከተው አካል ወስደው ከማፅደቅ ይልቅ፣በእንጥልጥል እንዲቆይ በማድረግ፣ከዚህ ብኋላ ግልፅነት በጎደለው መልኩ የድርጅቱ ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው እያዋሉ፣በከሳሾች ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ፡፡አልፎ ተርፎም ከሳሾች የስብሳበው ቃለ-ጉባኤ የኮምፒተር ፅሑፍ ከተፈረመ ብኋላ በሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ ብንጠይቅም እንዲሁም የሰነዱ ኪፒ ድርሻችንን ብንጠይቅም 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ስራ አስኪያጅ ከልክሎናል፡፡

በአጠቃላይ በከሳሾች እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉ ተከሳሾች መካከል ለረዥም ጊዜ የቆየ በድርጅቱ ስራ እና አሰራር ዙርያ ሊጠገን የማይችል ብርቱ አለመግባባትና እና ብርቱ ጭቅጭቅ አብሮ ለመስራት ብሎም ድርጅቱ ለማስቀጠል የማይቻልበት ደረጃ ደርሷል፡፡ከዚህ አኳያ ማህበሩ በንግድ ሕግ ቁጥር 218፣542 እና 543 እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 11 መሠረት እንዲፈርስ፣ከፈረሰም ብኋላ ሂሳቡ ተጣርቶ እንዲዘጋ እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች አለአግባብ ከድርጅቱ ለግል ጥቅማቸው ወጪ ያደረጉትን ገንዘብ በአንድነት እና በነጠላ ተመላሽ እነዲያደርጉ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል፡፡በማስረጃነትም የሰነድ ማስረጃዎች አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የተከሳሾች ጠበቃ በየካቲት 30 ቀን 2012 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ከሳሾች ዳኝነት የጠየቁበት ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ተከሳሾች እንዲከፍሉ በዚህ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም፤ የማህበሩ ገንዘብ ተከሳሾች ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን ተከትሎ ከሳሾች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ ከሳሾች እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር ስማችን የተጠቀሰው ተከሳሾች 1ኛ ተከሳሽ ድርጅትን በስምምነት መመስረታችን አይካድም፡፡በከሳሾች እንደተገለጸው በባለአክስዮኖቹ መካከል ለድርጅቱ ሰራተኞች የሚከፈለው ስራውን መሰረት ያደረገ የቦነስ ክፍያ ጋር በተያያዘ ብርቱ አለመግባባት መፈጠሩም የሚካድ አይደለም፡፡ኩባንያው በጅምር ያሉ ያላለቁ የበርካታ ደንበኞች ሥራዎች በእጁ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጅምር ስራዎች ሳይጠናቀቁ ኩባንያውን የማፍረስ ስራ ቢጀመር በነዚህ በርካታ ደንበኞቹ ላይ ከፍተኛ የእምነት መሸርሸር፣ እና መደናገጥ የሚፈጥር ከመሆኑ ባሻገር የከሳሾችንም ሆነ የተከሳሽን ጥቅም በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ ጅምር ስራዎቹ እስከሚጠናቀቁ ድረስ የማፍረስ ሂደቱ ቆይቶ ስራዎቹ ካለቁ በኋላ የኩባንያው ሂሳብ ተጣርቶ እንዲፈርስ ቢደረግ ተከሳሾችም የምንስማማበት ነው፡፡

የ2011 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሳብ ተሰርቶ ለመንግስት መከፈል የሚገባው ታክስ እና ግብር ተከፍላል፡፡ በዚህም መሰረት 1ኛ ተከሳሽ የንግድ ፈቃዱን ለማደስ የሚያስችለው ታክስ ክሊራንስ ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማግኘቱ የንግድ ፈቃዱን ለማሳደስ ችላል፡፡ ቀሪው ስራ የሂሳብ ሪፖርቱን ለኦዲተሮች አቅርቦ ማስጸደቅ እና በዚሁ መሰረት በመመስረቻ ጽሑፉ እና በንግድ ህጉ መሰረት ለባለአክስዮኖች መከፈል ያለበት የትርፍ ድርሻ ካለ በዚሁ መሰረት ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር ስማቸው የተጠቀሰው ተከሳሾች አዲስ ኩባንያው መክፈታቸው የሚካድ አይደለም፡፡ ሆኖም ተከሳሾች አዲስ ኩባንያ ያቋቋሙ እንጂ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ባላቸው ትልቅ ኃላፊነት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ በከሳሾችም ጭምር ተጀመረው ያልተጠናቀቁ በርካታ ጅምር ስራዎችን በማጠናቀቅ ስራ ላይ በመጠመዳቸው ምክንያት እንኳንስ የ1ኛ ተከሳሽን ደንበኞዎችን ሊወስዱ፣ ንብረት እና ሃብቱን ሊጠቀሙ እና ሰራተኞን አለአግባብ ሊያሰሩ ይቅርእና በግላቸው ያቋቋሙት ኩባንያን ስራ ለማስጀመር እንኳን አልቻሉም፡፡ከ2ኛ እስከ 4 ተራ ቁጥር ስማቸው የተጠቀሰው ተከሳሾች ከህግ እና አሰራር ውጪ የወሰዱት አንዳችም ገንዘብ በሌለበት ሁኔታ በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ በመሆን ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ክፈሉ ሊባሉ አይችሉም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡በማስረጃነትም የሠነድ እና የምስክሮች ስም ዝርዝር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

በተከሳሾች የቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያዎች በተመለከተ የከሳሾች ጠበቃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 145 መሰረት አስተያየት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡
ከሳሾች ያቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ ተመልክቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት በተከሳሾች የቀረበው መቃወሚያ መሰረት ያደረገው ተከሳሾች ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ገንዘብ በጋራ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል የሚል ነው፡፡የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ለመወሰን በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌደራል ፍርድ ቤቶች ያላቸው የዳኝነት ስልጣን በምን ጉዳይ ላይ እንደሆነ በአንቀጽ 3፣4 እና 5 ስር የተመለከተ ሲሆን ከእነዚህ የዳኝነት ስልጣን ውስጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በምን ጉዳይ ላይ እንደሆን በአንቀጽ 14 እና 15 ሥር ተመልክቷል፡፡
በተያዘው ጉዳይ ከሳሾች በ1ኛ ተከሳሽ ማህበር ላይ የመፍረስ ውሳኔ መሰጠቱን ተከትሎ የሂሳብ ማጣራት ሲከናወን ከ1ኛ-4ና የተጠቀሱት ተከሳሾች ለግል ጥቅማቸው የወሰዱን ገንዘብ መኖሩ ሲረጋገጥ ለማህበሩ ተመላሽ ሊያደርጉ ይገባል የሚል ዳኝነት ሲጠይቁ በከሳሾች ግምት ተከሳሾች እስከ ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ድረስ የማህበሩ ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል የሚል እንጂ ለከሳሾች ገንዘቡን እንዲከፍሉ የተጠየቀ ዳኝነት ባለመኖሩ ጉዳዩ ከዚህ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን በላይ ነው በማለት ተከሳሾች ያቀረቡት መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡
መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት የቀረበው መቃወሚያ ተከሳሾች ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ገንዘብ ማህበሩ መፍረሱን ተከትሎ የሂሳብ ማጣራት ሲከናወን ሲታወቅ ለማህበሩ ተመላሽ እንዲያደርጉ በሚል ዳኝነት መጠየቁ ከሳሾች የማህበሩ አባል በመሆናቸው ተከሳሾች በነበራቸው የሥራ አስኪጅነት እና የማህበሩ ሥራ መምራት ምክንያት በማህበሩ ላይ ያደረሱት ጉዳት ካለ በሂሳብ ባለሙያ እንዲረጋገጥ መጠየቅ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም የሚያስብል ሆኖ ፍርድ ቤቱ አላገኘውም፡፡
ፍርድ ቤቱም አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡
ከሳሾች በተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረቡት እና ዳኝነት የጠየቁት አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሊፈርስ ይገባል በማለት ሲሆን፣ ይህንኑ ዳኝነት የጠየቁትም በማህበሩ አባላት መካከል ብርቱ የሆነ አለመግባባት እና ጭቅጭቅ በመፈጠሩ ፣ ተከሳሾች ማህበሩ በተሰማራበት ተመሳሳይ ሥራ ላይ ድርጅት ከፍተው እየሰሩ በመሆኑ በፍርድ ቤቱ እንዲፈርስ በማለት ነው፡፡ተከሳሾች በአንዛሩ ማህበሩ የጀመራቸው ሥራዎች አጠናቆ እንዲፈርስ ውሳኔ ቢሰጥ ተቃውሞ እንደሌላቸው ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከሳሾች እና ከ2ኛ-4ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች የአድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባላት መሆናቸውንና ማህበሩም በህግ አግባብ የተቋቋመ ማህበር መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡
በሕግ አግባብ የተቋቋሙ የንግድ ማህበሮች ከተቋቋሙ በኃላ በህግ ወይም በፍርድ ቤት በሚሠጥ ውሣኔ ወይም በማህበርተኞች ስምምነት ሊፈርሱ እንደሚችሉ ስለንግድ ማህበሮች በጠቅላላው በሚደነግገው የንግድ ህጉ ክፍል ከቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሶስት የንግድ ማህበር ማፍረሻ መንገዶች እያንዳንዱ ራሱን ችሎ የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ የሚያደረግ ህጋዊ ውጤትን የሚያስከትሉ ሲሆን በእያንዳንዱ የንግድ ማህበር ማፍረሻ መንገድ የንግድ ማህበሮች የሚፈርሱበት ምክንያት ደግሞ የተለያየ መሆኑን ከላይ ከጠቀስናቸው ድንጋጌዎች መንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የንግድ ማህበር ማፍረሻ መንገዶች ውስጥ ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያለው በፍ/ቤት ውሣኔ አማካኝነት የንግድ ማህበሮች

የሚፈርሱበት አግባብ በመሆኑ ይህን የንግድ ማህበር ማፍረሻ መንገድ ለብቻ ከህጉ አኳያ መመልከቱ ተገቢ ነው።
የንግድ ማህበሮች በፍ/ቤት ውሣኔ አማካኝነት እንዲፈርሱ የሚደረገው ይህም ማለት ፍ/ቤት የንግድ ማህበሮች እንዲፈርሱ የሚወሰነው ከማህበርተኞች አንዱ ወይም የተወሠኑ ማህበርተኞች ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሠው የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጥያቄ /ክስ/ ሲያቀርቡ ነው ይህም ከን/ህ/ቁ 218/1/2/፣ 258/1/፣ 278/1/ረ/፣ 303፣ 495/1/ሠ/3/፣ 542/1/፣ 543/2/ ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል። ከዚህ ላይ ግን መታየት ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ ፍ/ቤት የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ የሚወስነው መቼ እና በምን ምክንያት ነው? የሚለው ጉዳይ ነው። በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ ባለአክሲዮን የሆነ ሠው በዚህ ማህበር ውስጥ በህግ የተረጋገጡለት የተለያዩ መብቶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ባለአክሲዮን የሆነበት የንግድ ማህበር እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት ነው። ማህበርተኛው ይህ መብት ያለው ቢሆንም ፍ/ቤቱ የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ የሚበይነው ግን እንዲሁ ማህበርተኛው ይህን መብቱን በመጠቀም ማህበሩ እንዲፈርስ ክስ ስላቀረበ ብቻ ሣይሆን የንግድ ማህበሩን ሊያስፈርስ የሚያስችል በቂ እና ትክክለኛ ምክንያት /Sufficient and good cause/ ያለ መሆኑን ማህበርተኛው ያስረዳ፣ ፍ/ቤቱም ማህበሩን ሊያስፈርስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ያለ መሆኑን ያረጋገጠ ወይም የተገነዘበ ከሆነ ብቻ ነው።ይህንም ከላይ ከጠቀስናቸው ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል። ከዚህ ውጪ የንግድ ማህበሮች ጥያቄ ስላቀረበ ብቻ ወይም በማንኛውም ምክንየት እንዲፈርሱ የሚደረግ /የሚወሰን/ ከሆነ በንግድ ህጋችን እንዲሁም በሌሎች ህጐቻችን፣ ህገ መንግስቱን ጨምሮ የንግድ ማህበሮች እንዲቋቋሙ፣ እንዲስፋፉ እንዲደረግ የተደነገገበትን አላማ፣ የንግድ ማህበሮች እንደአይነታቸው እና ባህሪያቸው ለይቶ በህግ ልዩ ጥበቃ መስጠት ያስፈለገበትን አላማ፣ ህግ አውጪው ለማህበርተኛው ማህበሩ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የሠጠበትን አላማ እንዲያሣካ የሚያደርግ አሉታዊ ውጤትን ያስከትላል።
የንግድ ማህበሮች በተለያዩ የንግድ፣ የኢኮኖሚ ስራዎች ላይ መሠማራት፣ መቋቋም ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ወሳኝ የሆነ ሚያ ያላቸው ሲሆን የሀገራት ኢኮኖሚ እድገትም ከንግድ ማህበሮች መቋቋም ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም የንግድ ማህበሮች መቋቋም፣ መስፋፋት ብሎም መፍረስ ከማህበርተኞች መብትና ጥቅም አልፎ በሶስተኛ ወገኖች /ለምሣሌ በሠራተኞች፣ ከማህበሩ ጋር የውል ግዴታ በሚገቡ ሠዎች በገንዘብ ጠያቂዎች ወዘተ.../መብትና ጥቅም ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ላይ አዎነታዊ/አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ የንግድ ማህበራት ጉዳይ በተለይም የንግድ ማህበራት መፍረስ ጉዳይ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ከአጠቃላይ የንግድ ህጉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።
በፍርድ ቤት ውሣኔ አማካኝነት የንግድ ማህበሮች እንዲፈርሱ ሊያስደርጉ /ሊያስወስኑ/ የሚያስችሉ በቂ እና ትክክለኛ ምክንያቶች ምን ምን እና ምን አይነት ውጤት ሊያስከትሉ የሚያስችሉ ምክንያቶች እንደሆኑ በን/ህ/ቁ 218/2/ ስር የተመለከተ ሲሆን የዚህን ድንጋጌ አቀራረጽ /ይዘት/ ስንመለከት ደግሞ ድንጋጌው የያዘው ዝርዝር ያለቀለት ዝርዝር /Exhuastive list/ ሳይሆን ያላለቀለት ዝርዝር /Illustrative list/ ነው። በመሆኑም በድንጋጌው ስር ያልተጠቀሰ ምክንያት እንደ በቂ ምክንያት ተደርጐ ሊወሠድ፣ በዚህ ምክንያትም ፍ/ቤቱ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል። ከዚህ ላይ በዋነኛነት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የቀረበው ምክንያት ማህበሩን ሊያስፈርስ የሚያስችል በቂ እና ትክክለኛ ምክንያት ተደርጐ ሊወሠድ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጭብጥ ሲሆን የቀረበው ምክንያት በቂ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ደግሞ ከላይ የገለጽነውን የህጉን አላማ፣ የንግድ ማህበሩ ህልውና መቆየት ከሚያስገኘው ጥቅም፣ ከሚያስከትለው ጉዳት አኳያ ሊታይ እና

ሊመዘን ይገባል፡፡ ማህበሩን ለማስፈረስ የቀረበው ምክንያት ወይም ችግር የንግድ ማህበሩ የተመሠረተበትን አላማ በሙሉ እንዲያሣካ ወይም ማሳካት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ያደረሰ ከሆነ፣ የንግድ ማህበሩ ህልውና መቆየት ከንግድ ማህበሮች መቋቋም እና መስፋፋት የሚፈለገውን እና የሚጠበቀውን አዎንታዊ ውጤት ማስገኘት /ማበርከት/ የማይችል፣ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ከሆነ የዚህ ማህበር ህልውና መቆየት፣ በማህበሩ፣ በማህበርተኞች እና በሶስተኛ ወገኖች መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ የቀረበው ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ሊያስወስን የሚያስችል በቂ እና ትክክለኛ ምክንያት ተደርጐ ሊወሠድ ይችላል፡፡ በመሆኑም ማህበሩን ለማስፈረስ የቀረበው ምክንያት በቂ እና ትክክለኛ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ ከዚህ አኳያ ሊታይ እና ሊመዘን ይገባል፡፡ የንግድ ማህበሩን ሊያስፈርስ የሚያስችል ከላይ የተገለፀው አይነት በቂ እና ትክክለኛ ምክንያት ያለ መሆኑን ደግሞ ማህበሩ እንዲፈርስ ጥያቄ /ክስ/ ያቀረበው ወገን /ከሣሽ/ በቅድሚያ የማስረጃት ሸክም አለበት /The one who alleges in the affirmative shall prove it/ ይህንም ስለማስረጃ ማቅረብ ግዴታ እና ስለአቀራረቡ ሁኔታ ከሚደነግገው ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2001 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ ማህበርተኛ የሆኑ ሠዎች መግባባት፣ በሠላም፣ በመተባበር መስራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ማህበሮቹም በአብዛኛው የሚተዋወቁ ሠዎች የሚያቋቁሙት በመሆኑ የንግድ ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ለማሣካት ይችል ዘንድ ማህበርተኞች በመግባባት፣ በመተባበርና ተገናኝቶ በመመካከር መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የንግድ ማህበሩ አባላት ተገናኝተው መወሰን እና ተግባብተው መስራት ያለባቸውን ስራ የሚያከናውን ከሆነ እና አባላቱም መገናኘትና ተነጋግረው መስራት ካልቻሉ ማህበሩ የተመሰረተበትን አላማ ሊያሣካ አይችልም፡፡ ማህበርተኞች ተባብረው መስራት ሲገባቸው ይህን ባለማድረጋቸው ምክንያት የንግድ ማህበሩ የተመሰረተበትን ስራ መስራት ካልቻለ፣ አሳካቸዋለሁ ብሎ በመመስረቻ ጽሑፍ ያስቀመጣቸውን አላማዎች በሙሉ ወይም በከፊል ማሳካት ካልቻለ የዚህ የንግድ ማህበር ህልውና መቆየት በማህበርተኞች፣ በማህበሩ፣ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ይህ ምክንያትም ማህበሩ እንዲፈርስ ሊያስወስን የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል፡፡

ከእነዚህ ከላይ ካየናቸው ሁኔታዎች አኳያ የያዝነውን ጉዳይ ስንመለከት ተከሳሾች አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መፍረስ ምክንያት የተደረገው ፍሬ ነገሮች አምነው ክርክር ከማቅረባቸውም በተጨማሪ በማህበሩ መፍረስ ላይ ልዩነት እንደሌላቸው ለፍርድ ቤቱ አረጋግጠዋል፡፡ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው የንግድ ማህበሩ የተመሰረተበትን እና በማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ያስቀመጣቸውን አላማዎች በአግባቡ በማሳካት ማህበርተኞችን፣ ሶስተኛ ወገኖችን ተጠቃሚ ማድረግ ይችል ዘንድ ማህበርተኞች በመተባበር አብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማህበርተኞች ይህን ማድረግ ሲገባቸው ሳያደረጉ በመቅረታቸው ማህበሩ ስራውን መስራት ካልቻለ የዚህ ማህበር ሕልውና መቆየት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የንግድ ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ማሳካት ካልቻለ በዚህ ሁኔታ የንግድ ማህበሩ የሚቀጥልበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ ይህ ምክንያትም የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊያስወስን የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ ፍርድ ቤቱም አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በንግድ ሕግ ቁጥር 218 /1//2/፣ 542/1/ መሠረት እንዲፈርስ በማለት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሣኔ

1. አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲፈርስ ተወስኗል፡፡

2. ግራ ቀኙ የማህበሩ መፍረስ ተከትሎ የሂሳብ አጣሪ በስምምነት መርጠው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የሂሳብ አጣሪ /Liquidator/ ሊመደብ ይገባል ተብሏል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት የወጣ ወጪና የደረሰ ኪሣራ ካለ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ተብሏል፡፡
ት ዕዛዝ
• አድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መፍረሱን ተከትሎ ሂሣብ እና የስራ እንቅስቃሴ የሚመረምር ልምድ እና ፈቃድ ያለው እንዲሁም የተመሰከረለት ኦዲተር በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በኩል እንዲመደብ ታዟል፡፡
• በሬጅስትራር የሚመደበው የተመሰከረለት ኦዲተር የአድ ሆክ የማማከር እና ሥልጠና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሂሣብ በአጭር ጊዜ በማጣራት ሪፖርቱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡
• ይግባኝ ለጠየቀ መዝገቡ ተገልብጦ ይሠጠው፡፡
መዝገቡ በውሳኔ እልባት ስላገነ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት፡፡